የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

# AFAR REGION NEGARIT GAZETA

## OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሰባተኛ ዓመትቁጥር
ሠመራ ሰኔ **30** ቀን **1994** ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**14th Year No. 17**
**Samara July ,2002**

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ---------- ገጽ **1**

አዋጅ ቁጥር **17/1994** ዓ ም

## የአፋር ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የክልል ም/ቤት አስፈፃሚው አካል የአሠራር ተፅዕኖ ተላቆና ራሱን ችሎ እንዲዋቀርም ሆነ የራሱን ነፃ አመራር እንዲኖረው በተሻሻለው የ 1994 ዓ.ም ሕገ መንግስት የተወሰነ በሆኑ፣

በዚህም የተነሳ የክልል ም/ቤቱ በሕገ መንግስቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ይቻለው ዘንድ ፈርጀ የራሱን ጽ/ቤት፣ ማደራጀትና ሥልጣንና ተግባሩን በህግ መወሰን ተገቢ ሆኖ በመገኘት፣

እንዲሁም በክልሉ ውስጥ የህዝብ አስተዳደርን፣ የወረዳና የቀበሌ ም/ቤቶች የዕለት ከዕለት አሠራርና ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በዚሁ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት አማካኝነት መከታተልና መደገፍ የማይታለፍ ተግባር ሆኖበመገኘቱ፣

የአፋር ብሔራዊ ክልል ም/ቤት በ 1994 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌ

**አንቀጽ 1.** አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 17/1994 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ክፍል ሁለት

አንቀጽ **2.** ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. «የክልል ምክር ቤት» ማለት በ 1994 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የአፋር ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ ---------- ስር የተቋቋመውና ዝርዝር ስልጣንና ተግባሩ የተገለፀው አካል ነው።
2. «አፈ-ጉባኤ» ማለት ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ሕገ መንግስት አንቀጽ ------ ንዑስ አንቀጽ ------- መሠረት ከክልሉ ም/ቤት አባላት መካከል ተመርጣ ለም/ቤቱ የሥራ ዘመን እንዲያገለግል የተሰየመ ባለስልጣን ወይም የሕዝብ ባለአደራ ሲሆን እንደአግባብነቱ የክልል፣ የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች አፈ-ጉባኤዎችንም ይጨምራል።
3. «ጽ/ቤት» ማለት የክልል ም/ቤቱ ጽ/ቤት ነው።

ክፍልሶስት

ስለክልሉ ም/ቤት ጽ/ቤትመቋቋም፣ዓላማ፣አደረጃጀትና ተልዕኮ

አንቀጽ **3** ስለመቋቋም

1. የአፋር ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት ከዚህ በኋላ ጽህፈት ቤቱ እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ተጠሪነቱ ለአፈ-ጉባኤው ይሆናል።

አንቀጽ **4** ዓላማ

የጽ/ቤቱ ዓላማ ም/ቤቱና አመራሩ በሕገ-መንግስቱ የተጣለባቸውን ሕዝባዊ አደራና ኃላፊነት በብቃትና በታማኝነት ተልዕኳቸውን እንዲወጡ ማስቻልና ማሳካት ነው።

አንቀጽ **5** የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት በመሆን ያገለግላል፣
2. ለክልሉ ም/ቤትና ልዩ ልዩ ኮሚቴዎቹ ሁለገብ አገልግሎት ይሠጣል፣
3. ለክልሉ ም/ቤትና ኮሚቴዎቹ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ያሰናዳል፣ያደራጃል፣ የመገልገያ ቁሳቁሶችን ያሟላል፣
4. የም/ቤቱና ኮሚቴዎቹ ቃለ ጉባኤዎች፣ ውሳኔዎችና ሰነዶች በሚገባ ተመዝግበው እንዲያዙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣
5. ለክልሉ ም/ቤት አባላትና አካላቱ የቤተ መጽሀፍት፣ የምርምርና የመረጃ አገልግሎት ይሠጣል፣
6. የክልሉ ም/ቤት በየጊዜው የሚያወጣቸው አዋጆችና ደንቦች በቅርጽም ሆነ በይዘት በወቅቱ ተሟልተውና ተስተካክለው በክልሉ ነጋሪት ጋዜጣ እንዲታተሙና ለሚመለከታቸው አካላትም ሆነ ለተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች እንዲሰራጩ ያደርጋል፣
7. በክልሉ ም/ቤት የሚወጡ ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና በራሪ ጽሁፎች ዝግጅት ህትመትና ስርጭት ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣
8. ከአፈ-ጉባኤው በሚሰጠው አመራር መሠረት የም/ቤቱን አባላትና ተጋባዥ እንግዶችን ይቀበላል፣ ተፈላጊው የመስተንግዶ አገልግሎት ተሟልቶ የቀረበላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣

9. የክልሉን ም/ቤት ጨምሮ የየደረጃው ም/ቤት አባላት አቅም የሚጐለብትበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ይደግፋል፣
10. በተዋረድ ጽ/ቤቶች የሚሠሩ ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን አያያዝና አስተዳደር በበላይነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
11. ምክር ቤቱ ያሳለፋቸው ውሳኔዎች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፣
12. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣
13. የክልሉን ም/ቤት ሥራ ለማሳካት የሚረዱና በአፈጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

**አንቀጽ 6** ስለ ጽ/ቤቱ አደረጃጀት፣አመራርና ተጠሪነት

1. ጽ/ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተዘረዘሩትን ተግባርና ኃላፊነቶቹን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልገውን ድርጅታዊ መዋቅር አጥንቶ በአፈጉባኤው አማካኝነት ያስወስናል፣
2. ጽ/ቤቱ በክልሉ ም/ቤት አፈ-ጉባኤ በሚሾም አንድ የበላይ ኃላፊ ይመራል፣ ይተዳደራል፣
3. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለአፈ ጉባኤው ይሆናል።

**አንቀጽ 7** የጽ/ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

የጽ/ቤቱ ኃላፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ስር ለጽሕፈት ቤቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣
2. ከአፈ ጉባኤው በሚሰጠው አመራር መሠረት የጽ/ቤቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣
3. የጽ/ቤቱን ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ሕጐችና ደንቦች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣
4. የጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ኘሮግራም አዘጋጅቶ ለአፈ ጉባኤው ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
5. የጽ/ቤቱን ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፣ የተፈቀደውን በጀት መሠረት የፋይናንስ ሕግን መሠረት አድርጐ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣
6. ከአፈ ጉባኤው በሚሰጠው አመራር መሠረት ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽህፈት ቤቱን ይወክላል፣
7. የጽህፈት ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርት ለአፈ ጉባኤው ያቀርባል፣
8. በአፈ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፣
9. ለሥራ ቅልጥፍና ሲባል ከተግባሩ ከፊሉን በውክልና ለጽ/ቤቱ የበታች የሥራ ኃላፊዎችና ለሌሎች ሊያስተላልፍ ይችላል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 8** በጀት

የጽህፈት ቤቱ በጀት በክልሉ ም/ቤት የሚመደብ ይሆናል።

**አንቀጽ 9** የሂሳብ መዛግብት

1. ጽህፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣
2. የጽህፈት ቤቱን የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር አማካኝነት በየጊዜው ይመረመራሉ።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማናቸውም ጊዜና ሁኔታ አፈ ጉባኤው የጽ/ቤቱ ሂሳብ ወይም ንብረት ነክ መዛግብትና ሠነዶች በልዩ ሁኔታ እንዲመረመሩ ሊያዝ ይችላል።

አንቀጽ **10** የተፈፃሚነት ወሰን

1. አግባብነት ያላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በተዋረድ ም/ቤቶች ጽ/ቤቶች ኃላፊዎችና አሠራር ላይ እንደአስፈላጊነቱ ተፈፃሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ።
2. የየደረጃው ም/ቤቶች ሕገ መንግስታዊ አቃምና የአሠራር ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ የም/ቤት ጽህፈት ቤታቸውን ለዚህ አዋጅ አላማና አፈፃፃም የክልል ም/ቤት ጽ/ቤት ቅርንጫፎች ናቸው።

አንቀጽ **11** ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፃም የሚያስፈልጉትን ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ **12** አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ---------- ቀን **1994** ዓ.ም

እስማኤል አሊ ሴሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር